# አንድ የመንግሥት ወዳጅ
## ደራሲ ዚገፍሪድ ሌንስ

በአንድ የሳምንት መጨረሻ ላይ መንግሥት ምን ያህል ወዳጆች እንዳሉት ለማሳየት ባለሥልጣናቱ አንድ አካባቢን እንዲጎበኙ ጋዜጠኞችን ይጋብዛሉ። ሰላም የለውም እየተባለ ስለእዚያ ክልል የሚጻፈው ነገር ሁሉ እውነት እንዳልሆነ ሊያረጋግጡልን ፈልገዋል። ግርፋት የለም፤ ድህነት፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ ነፃ እንውጣ የሚል ቁጣ ያዘለ ፍላጎት የለም። እናም በጣም በአክብሮት ጋበዙን። አንድ በጣም ትህትና የተላበሰ፤ ሽክ ያለ የመንግሥት ባለሟል ከኦፔራው ህንፃ በስተጀርባ ተቀበለንና ወደ ተዘጋጀው የመንግሥት አውቶብስ መራን። አውቶብሱ አዲስ ነው። የትኩስ ቫርኒሽ እና የቆዳ ሽታ ተቀበለን። ለስለስ ያለ ሙዚቃ ይሰማል። አውቶብሱ መንቀሳቀስ ሲጀምር የመንግሥት ባለሟሉ መነጋገሪያውን ከተቀመጠበት ብድግ አድርጎ ብርማ መሸፈኛውን በጥፍሩ በማንሳት ለስለስ ባለ ድምፅ፣ ‹‹በድጋሚ እንኳን ደህና መጣችሁ!›› አለን። ስሙንም አስተዋወቀን፤ ‹‹ስሜ ጋሬክ ይባላል›› በማለት። በመቀጠል ስለዋና ከተማዋ ውበቶች ጠቀሰልን። የመናፈሻዎቹን ስምና ብዛት፣ በጠዋት ድንግዝግዝ ብርሃን ኖራማው ጉብታ ላይ ስለሚታየው የናሙና ሰፈራ መንደር ግንባታ አይነት ገለፀልን። ከከተማው ውጭ መንገዱ መንታ መንገድ ይሆናል።

የባህሩን ዳርቻ እየተውን ድንጋይ የሞላባቸውን መስኮችና ቡናማ አቀበቶች አልፈን ገጠር ውስጥ ገባን። ከዛም ወደ አንድ ሰርጥ ገባንና በደረቀ ወንዝ ላይ የተዘረጋ ድልድይ ዘንድ እስክንደርስ ድረስ ውስጥ ውስጡን ተጓዝን። ድልድዩ ወደ አንድ የደረቀ ወንዝ ይመራል። ድልድዩ ላይ የነፍስ ወከፍ መሣሪያውን በግዴለሽነት የያዘና በአጠገቡ ስናልፍ በደስታ ሰላምታ የሰጠን አንድ ወጣት ወታደር ቆሟል። በደረቀው ወንዝ ውስጥ በታጠቡት ጠፍጣፋና ክብ ድንጋዮች መካከል ሁለት ወጣት ወታደሮች ቆመዋል። ጋሬክም በአንድ በጣም በታወቀ ወታደራዊ ልምምድ የሚካሄድበት ቦታ እያለፍን መሆኑን ነገረን።
ጠመዝማዛውን መንገድ ጨርሰን በአንድ ሞቃታማ ለጥ ያለ ሜዳ ላይ አለፍን። በተከፈቱት የጎን መስኮቶች የኖራ አቧራ ገባ። አይናችንን አቃጠለን። በከንፈሮቻችን ላይ የኖራ ጣእም
ተሰማን። ኮቶቻችንን አወለቅን። ጋሬክ ብቻ ኮቱን እንደለበሰ ነው። አሁንም መናገሪያውን በእጁ ይዞ ለስለስ ባለ አንደበት መንግሥት ለዚህ ህይወት አልባ መሬት ያቀደውን የልማት
እቅድ አብራራልን። አጠገቤ የተቀመጠው ሰው አይኖቹን ጨፍኖ አንገቱን ወደ ኋላ ዘንበል እንዳደረገ አየሁ። ከንፈሮቹ ደርቀው በኖራ ብናኝ ነጥተዋል። ብርማ የተቀባው የወንበሩ መደገፊያ ላይ ያረፉት የእጆቹ ደም ስሮች ሰማያዊ ሆነው ተወጣጥረዋል።

በሾፌሩ የኋላ መመልከቻ መስታዎት የጋሬክ ብቸኝነት የዋጣቸው አይኖች ደጋግመው ወደ እኛ ስለሚወረወሩ ነካ አድርጌ ልቀሰቅሰው ነበር። ይህንኑ ሳሰላስል ጋሬክ ከመቀመጫው ተነሳና በፈገግታ በካርቱን የታሸገ ቀዝቃዛ መጠጥ ከመምጠጫ ቀሰሞች ጋር እያደለን በጠባቡ መተላለፊያ መጣ። እኩለ ቀን ላይ በአንድ መንደር ውስጥ አለፍን። የመንደሩ ቤቶች በጣውላ እንጨት ተከርችመዋል። ከደረቅ ቅርንጫፍ የተሠሩት ቆሻሻ አጥሮች ተሸነቋቁረው ከሜዳው በሚነፍሰው ንፋስ ሳቢያ እዚያና እዚህ ተጣመዋል። በጠፍጣፋ  ጣራዎቻቸው ላይ ምንም ልብሶች እንዲደርቁ አልተሰጡም። የውሃ ጉድጓዱ ተከድኗል። አንድም የውሻ ጩኸት
አልተከተለንም። የትኛውም ቦታ አንድም ሰው አላየንም። አውቶብሱ ፍጥነቱን ሳይቀንስ የምርኮ ባንዲራ ይመስል ከኋላው ግራጫ አቧራ እያውለበለበ አለፈ።

ጋሬክ እንደገና በጠባቧ መተላለፊያ በመምጣት ሳንድዊቾች እያደለን ከግባችን ለመድረስ ብዙ እንደማይቀረን እየነገረን በትህትና መንፈሳችንን አነቃቃው። ገጠሩ ኮረብታማ ሆኗል።

ዝገታም ቀይ፣ በመካከላቸው ትናንሽ ቀለም አልባ ቁጥቋጦዎች በበቀሉባቸው ትላልቅ ቋጥኞች ተሸፍኗል። መንገዱ አቆለቆለና በመሬት ውስጥ መተላለፊያ አድርገን አለፍን። በፍንዳታ በግማሽ ክብ የተቦደሱት ቀዳዳዎች አግድሞሽ ጥላዎቻቸውን በቋጥኙ
ግድግዳ ላይ አጥልተዋል። አንድ ኃይለኛ ሙቀት አውቶብሱ ውስጥ ዘልቆ ገባ። ከዚህ በኋላ መንገዱ ሰፊ ሆነ። እናም በአንድ ወንዝ የተከፈለውን ሸለቆ አየነው። ከወንዙ ዳርቻም መንደሩን። ጋሬክ እንድንዘጋጅ የሚያሳስብ ምልክት ሰጠን። ኮቶቻችንን ለባበስን። አውቶብሱም ፍጥነቱን ቀንሶ አዲስ ኖራ ከተቀባ ጎጆ ፊት ለፊት፣ሸክላ ከተነጠፈበት አደባባይ ላይ ቆመ። ኖራው አይን እስኪወጋ ድረስ ያንፀባርቅ ነበር። አውቶብሱ ጥላውን ባሳረፈበት በኩል ሆነን ሲጋራዎቻችንን ወደ ጎን ወረወርን። አይናችንን አንጨፍርረን ወደ ጎጆው እየተመለከትን ወደ ውስጥ ገብቶ የተሰወረውን ጋሬክን መጠባበቅ ጀመርን። ተመልሶ እስኪመጣ ጥቂት ደቂቃዎች ወሰደ። ተመልሶ ሲመጣ ግን ማናችንም ከዚህ በፊት አይተነው የማናውቀውን ሰው ይዞ መጣ።

ይህ ቤላ ቦንትሶ ነው›› አለ ጋሬክ ወደ ሰውዬው እያመለከተ። ‹‹አቶ ቦንትሶ ቤት ውስጥ ሥራ ላይ ነበር። ይሁን እንጂ ማንኛውንም ጥያቄያችሁን ለመመለስ ዝግጁ ነው›› ሲል
አከለበት። እይታችንን ባለመድፈር ፊቱን በትንሹ ጎንበስ ወዳደረገው ቦንትሶ በቅንነት ተመለከትን። የሽማግሌ ገፅታ አለው። ግራጫ አቧራማ። አንገቱ ላይ ጥልቅ የሆኑ ጥቋቁር
ሽብሸባቶች ተሰምረዋል። የላይኛው ከንፈሩ አብጧል። ከሥራው ላይ ድንገት ብድግ ብሎ የመጣው ቦንትሶ ፀጉሩ በደንብ የተበጠረ ሲሆን በከሲታው የሽማግሌ አንገቱ ላይ የተረጨት የደረቁ የደም ነጠብጣቦች በችኮላና በጥንቃቄ የተካሄደ የፂም መላጨት ምስክሮች ናቸው። ንፁህ የጥጥ ሸሚዝና ቁርጭምጭሚቱ ጋር ለመድረስ ያልቻለ አጭር የጥጥ ሱሪ ለብሷል። እግሮቹ ልክ ምልምል ወታደሮች በስልጠና ወቅት እንደሚጫሚቸው ባሉ አዲስ ካልለፋ ቆዳ በተሠሩ ቢጫ ቡትስ ጫማዎች ተሸፍነዋል።

ለቦንትሶ ሰላምታ ሰጠነው። እያንዳንዳችንም ጨበጥነው። እጅ ነሳንና ወደ ቤቱ መራን። ከሱ ቀድመን ወደ ውስጥ እንድንገባ ጋበዘን። አንድ አሮጊት ሴትዮ ትጠብቀን ወደ ነበረበት
ቀዝቃዛ ጎጆ ገባን። ገፅታዋን መለየት አይቻልም። ጨለም ባለው ብርሃን የሚያበራው ያሰረችው ሻሽ ብቻ ነበር። ሴትየዋ ጭብጥ ጭብጥ የሚያክሉ እንግዳ የሆኑ ፍራፍሬዎች ሰጠችን። ፍራፍሬዎቹ በመጀመሪያ ትኩስ ቁስል የነከስኩ አይነት ስሜት እንዲሰማኝ ያደረጉ ቀይ ብርሃንማ ስስ ቆዳ አላቸው። ተመልሰን ሸክላ መሰል ንጣፍ ወዳለው አደባባይ ወጣን።
ከአውቶብሱ አጠገብ ባዶ እግራቸውን የሆኑ ልጆች ቆመዋል። መቋቋም እስኪያቅተው ድረስ ትክ ብለው ቦንትሶን ይመለከቱታል። ይህን ሲያደርጉ እርስ በእርሳቸው አይነካኩም፤አይነጋገሩም። አንዳቸውም እኛን አያዩም። ቦንትሶ ሚስጥራዊ በሆነ የእርካታ ስሜት ፈገግ አለ። ‹‹ልጆች የለዎትም?›› ሲል ፖትጊሰር ጠየቀ። የመጀመሪያው ጥያቄ ነበር። ቦንትሶ በፈገግታ መመለስ ጀመረ። ‹‹በሚገባ! በሚገባ! አንድ ልጅ ነበረን። አሁን ግን ልንረሳው እየሞከርን ነው። በመንግሥት ላይ አምፆአል። ሠነፍ ነበር። ከንቱ። እናም ትልቅ ሰው መሆን ፈልጎ በየቦታው አመፅን ከሚያስነሱት አሻጥረኞች ጋር ተቀላቀለ። ከመንግሥት
ጋር የሚዋጉት እኮ የተሻለ ነገር ማድረግ ይቻላል ብለው ስለሚያምኑ ነው።›› ቦንትሶ በዝግታ ሲናገር ጉዳዩ ትኩረት የሚያሻው መሆኑን እያሰመረበት ነበር። እየተናገረ እያለ የፊት ጥርሶቹ የወለቁ መሆናቸውን ተመለከትኩ። ምናልባትም እኮ! የተሻለ ነገር ያመጡ ይሆናል።›› አለ ፖትጊሰር። ጋሬክ ጥያቄውን እንደሰማ በደስታ ፈገግ አለ።
ቦንትሶ መናገር ጀመረ። ሁሉም መንግሥታት እዚህ ላይ ይመሳሰላሉ። የሰው ልጅ ሊሸከማቸው ግድ ነው። ለአንዱ ይቀላሉ፣ለሌላው ይከብዳሉ። ይህንን መንግሥት እናውቀዋለን። ስለ ሌሎቹ የምናውቀው ነገር ቢኖር ቃል ኪዳኖቻቸውን ብቻ ነው።›› ልጆቹ
እርስ በእርስ ተያዩ። ምንም ቢሆን ተደጋግሞ የሚሰጠው ትልቁ ተስፋ የነፃ መውጣት ጉዳይ ነው።›› አለ ብላይጉት።

‹‹ነፃነትን ሰው ሊበላው አይችል!›› አለ ቦንትሶ በፈገግታ፤

‹‹አገራችን ወደ ድህነት አዘቅት እየወረደች ነፃነት ለኛ ምን ይጠቅመናል!? ይህ መንግሥት ግን ወደ ውጭ የምንልካቸውን ምርቶች አስተማማኝ አድርጓል። መንገዶች፣ የጤና ጣቢያዎች እና ትምህርት ቤቶች እንዲገነቡ አድርጓል። መሬት እንዲታረስ
አድርጓል። ወደ ፊት ገና ብዙ እንዲታረስ ያደርጋል። በተጨማሪም የመምረጥ መብትን ሰጥቶናል።›› በልጆቹ መካከል የመንቀሳቀስ ነገር ታየ። እጃቸውን አያያዙና ሳያስቡት አንድ እርምጃ ወደ ፊት ተራመዱ። ቦንትሶ አንገቱን ደፋ። ምስጢራዊ በሆነ እርካታ ፈገግ አለ።
አንገቱን እንደገና ቀና እንዳደረገ በአይኑ ከኋላችን የቆመውን ብዙም ደስተኛ ያልሆነውን ጋሬክን ፍለጋ ገባ። ‹‹በመጨረሻም›› አለ ቦንትሶ ሳይጠየቅ፣ ‹‹ከነፃነት ጋር የሆነ የመብሰል ነገር ያስፈልጋል። ምናልባትም ነፃ መውጣትን በፍፁም መጀመር አንችል ይሆናል። ሕዝቦችም ቢሆኑ እኮ የሚበስሉበት ጊዜ አለ። እኛ እዚህ እድሜ ላይ ገና አልደረስንም። እኔ ደግሞ አለመብሰላችንን መና ያላስቀረው የዚህ መንግሥት ወዳጅ ነኝ። በደንብ ማወቅ ከፈለጋችሁ ለዚህ ምስጋና አቀርባለሁ።›› ጋሬክ ወደ አውቶብሱ ዘንድ ሄደ። ቦንትሶ
በአትኩሮት ይከታተለዋል። ከባዱ የአውቶብስ በር ጓ! ብሎ እስኪዘጋና እዚያ የደረቀ የሸክላ ንጣፍ ላይ ብቻችንን እስክንሆን ጠበቀ። ያለነው እኛ ብቻ ነበርን። እናም ከሬዲዮ ጣቢያ
የመጣው ፊንከ ወደ ቦንትሶ ዞሮ በፈጣን ጥያቄ፣ ‹‹እውነቱ እንዴት ነው? ቶሎ በል ብቻችንን ነው ያለነው›› አለው። ቦንትሶ ምራቁን ውጦ ፊንከንን በመገረምና እንግዳ በሆነ ስሜት ተመለከተውና ቀስ ብሎ ‹‹ጥያቄዎ አልገባኝም!›› አለው። ‹አሁን በግልፅ መናገር እንችላለን።›› አለ ፊንከን ፈጠን ብሎ።

‹በግልፅ መነጋገር?›› ደገመው ቦንትሶ። ትንፋሽ ወሰደና የወለቁት ጥርሶቹ በደንብ እንዲታዩ በሰፊው ፈገግ ብሎ፣ ‹‹የነገርኳችሁ ነገሮች በበቂ ግልፅ ናቸው። እኛ የዚህ መንግሥት ወዳጆች ነን። እኔና ባለቤቴ። ምክንያቱም ለደረስንበት ለዚህ ደረጃ የበቃነው በእሱ እርዳታ ነው። ስለዚህም እናመሰግነዋለን። መቼም ያውቃሉ፤ አንድ ሰው መንግሥትን ስለሆነ ነገር
ማመስገን ሲችል ብዙ ጊዜ አይታይም፤ እኛ ግን እናመሰግነዋለን። ጎረቤቴም ያመሰግነዋል፤ እዚያ ያሉት ልጆች ጭምር፤ የቀዬው ፍጥረት ሁሉ። እያንዳንዱን በር አንኳኩ። ከሁሉም የምትሰሙት መንግሥትን እንዴት አድርገን እንደምናመሰግነው ነው።››

ገርጣ ያለው ወጣት ጋዜጠኛ ጉም ድንገት ወደ ቦንትሶ ቀረብ ብሎ፣ ‹‹አንድ እውነተኛ መረጃ አለኝ። ልጅዎ እንደተያዘና ዋናው ከተማ ውስጥ የሚገኝ እስር ቤት ታስሮ እየተገረፈ
እንደሆነ የሚገልፅ። ስለዚህ ምን ይላሉ?›› ሲል አንሾካሾከለት። ቦንትሶ አይኖቹን ጨፈነ። የአይኑ ሽፋሽፍት ላይ የኖራ ብናኝ አለ። በፈገግታ እንዲህ ሲል መለሰ። ‹‹ምንም ልጅ
የለኝም። ስለሆነም ሊገረፍ አይችልም። እኛ መንግሥትን እንደግፋለን ይሰሙኛል!? እኔ የመንግሥት ወዳጅ ነኝ።›› በእጅ የተጠቀለለ የጎበጠ ሲጋራ አቀጣጠለ። በረጅሙ
ሳበና አሁን ወደተከፈተው የአውቶብስ በር አቅጣጫ ተመለከተ። ጋሬክ ተመልሶ መጣና ስለ ውይይቱ ጠየቀ። ቦንትሶ በቆመበት ሆኖ በእግሮቹ ጣቶችና ተረከዞች እየተደገፈ ወደፊት ወደኋላ ይወዛወዛል። ጋሬክ ሲቀላቀለንና የሲጋራውን ጭስ በወለቀው ጥርስ በኩል አልፎ አልፎ በምሬት እያስወጣ ጥያቄያችንን በቀልድ እያዋዛ በዝርዝር ሲመልስ ታማኝ፣ ሸክሙ የቀለለውና እፎይ ያለ ይመስላል።

አንድ ረጅም ማጭድ የያዘ ሰው በአጠገባችን ሲያልፍ ቦንትሶ ጠራው። ሰውዬው በዝግታ እየተራመደ ቀረበ። ማጭዱን ከትከሻው አወረደና እኛ ቀደም ሲል ለእሱ አቅርበንለት
የነበረውን ጥያቄዎች ከቦንትሶ አፍ መስማት ጀመረ። ሰውዬው በቁጣና በመገረም ስሜት ራሱን ነቀነቀ። ጥልቅ ስሜት ያለው የመንግሥት ወዳጅ ነበር። እያንዳንዱ ሀሳቡን ቦንትሶ ዝምታ በዋጠው ድል ያረጋግጣል። በመጨረሻም ሰዎቹ እኛ ባለንበት ከመንግሥት ጋር ያላቸውን ትስስር ለማረጋገጥ

በሚመስል እጅ ለእጅ ተያያዙ። እኛም መሰናበት ጀመርን። እያንዳንዳችን በንትሰን ጨበጥነው። እኔ የመጨረሻው ነበርኩ። ሻካራውንና የተዘረጋው

እጇን ስጨብጠው በእጆቻችን መካከል የተጣጠፈ ወረቀት ተሰማኝ። ቀስ ብዬ ጣቶቼን ጨብጬ ያዝኩት። መለስ ብዬ ወረቀቱን እኪሴ ውስጥ ከተትኩት። ቤላ በንትሶ እዚያው ቆሞ ትምባሆውን በፍጥነት ማግ ማግ ያደርጋል። ሚስቱን ጠራት። ልጆቹ ቀለም አልባ በሆኑ ቁጥቋጦዎች ወደተሸፈነው ኮረብታ ሲወጡ እሷ፣ በንትሰና ረዥም ማጭድ የያዘው ሰውዬ ደግሞ የሚጓዘውን አውቶብስ ይመለከቱ ነበር።

በመጣንበት መንገድ ተመልሰን አልተጓዝንም። ከዛ ይልቅ በአጠገቡ አንድ ጥርጊያ መንገድ የሚያልፍበትን የባቡር ሀዲድ ዳርቻ እስክናገኝ ድረስ ሞቃታማውን ቦታ አቋረጥን። በዚህ የጉዞ ወቅት አንድ እጄን ኪሴ ውስጥ አድርጌው ነበር።እጄ ደግሞ በጥፍሬ በጣም ብጫነውም እንኳን ሊለመጥ ያልቻለ ጠጣር ነገር የያዘውን ወረቀት ይዟል። ወረቀቱን ከኪሴ

ለማውጣት አልደፈርኩም። ምክንያቱም አሁንም አሁንም የጋሬክ በብቸኝነት የተዋጠ እይታ በአውቶብሱ የኋላ መመልከቻ መስታዎት እየደረሰን ነው። የሚያስፈራ ጥላ በላያችን ላይ

አንዣቦ በህይወት አልባው መሬት ላይ አለፈ። ከዚያ በኋላ ዝቅ ብሎ በባቡር ሀዲዱ ዳርቻ ወደ ዋናው ከተማ የሚበረውን የአውሮፕላን ድምፅ ሰማን። አድማሱ ጠርዝ ሲደርስ ተጠማዘዘና እኛ የምንሄድበትን መንገድ ተከትሎ አብሮን ይበር ጀመር። ስለ ቤላ በንትስ አሰብኩ። የተጣጠፈውን ጠንካራ ነገር የያዘውን ወረቀት በእጄ ይዣለሁ። መዳፌ ምን ያህል እንደረጠበ ተሰማኝ። ከሀዲዱ ዳርቻ የሆነ ነገር ወደኛ ሲመጣ ተመለከትን። በጣም ሲቀርበን ወጣት ወታደሮች የተሳፈሩበት አንድ ፉርጎ እንደሆነ ተመለከትን። ጠመንጃቸውን በማንሳት ሰላምታ ሰጡን። ቀስ ብዬ ወረቀቷን አወጣኋት። ከፍቼ ግን አላየኋትም ቶሎ ብዬ

የውስጥ የደረት ኪሴ ውስጥ ከተትኳት። መቆለፍ የምችለው ብቸኛ ኪሴ እሱ ነው። እንደገና ስለ መንግሥት ወዳጁ ቤላ በንትሶ ማሰብ ጀመርኩ። እንደገና ቢጫ ካልለፋ ቆዳ የተሠራ

ጫማውን፣ የህልም አይነት የውስጥ እርካታ ገፅታውንና መናገር ሲጀምር የሚታዩትን የወላቃ ጥርሶቹን ክፍተት አያለሁ። ከመካከላችን ማንም በእሱ ውስጥ ደስተኛውን የመንግሥት ወዳጅ ስለማግኘታችን አይጠራጠርም። ባህሩን ተከትለን ወደ ዋናው ከተማ ተመለስን። ንፋሱ ከቋጥኙ ግርጌ ጋር የሚላጸማን ውሃ ሹክሹክታ ያደርሰናል። ከኦፔራው ህንፃ ዘንድ እንደደረስን ከአውቶብሱ ወረድን። ከጋሬክ ጋር በአክብሮት ተለያየን። ለብቻዬ ወደ ሆቴልተመልሼ ሄድኩና አሳንሰሩን ተጠቅሜ ወደ ክፍሌ ሄድኩኝ። ሽንት ቤት ገባሁና የመንግሥት ወዳጁ በሚስጥር ያቀበለኝን ወረቀት ከፈትኩት። ምንም አልተጻፈበትም። ምንም ምልክት፤ ምንም ቃል አልሠፈረበትም። ሆኖም ግን ወረቀቱ ውስጥ አንድ

ጭስ ያበለዘው የፊት ጥርስ ተጠቅሏል። የሰው የተሰበረ ጥርስ። እናም የማን ጥርስ እንደነበር አውቄያለሁ።